ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም

<u>የቤት ሽያጭ ውል</u>

ውል ሰጪ----------ወ/ሮ ብርቁ በዳዳ

አድራሻ፣ ሱሉልታ ሙሎ ወረዳ ወሰርቤ ዱቱ ቀበሌ ገበሬ ማህበር

ውል ተቀባይ----------1. አቶ በላይነህ ጌታቸው

አድራሻ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የቤት.ቁ 047

ውል ሰጭና ውል ተቀባይ ተብዱ በዚህ ውል የምጠራው በፍ/ብሄር ህግ ቁጥር 1711/17331/2005/226/2273/1.2.7 መሰረት ውል ተስማምተን ፈርመናል።

1. ውል ሰጪ በሱሉልታ ሙሎ ወረዳ ወሰርቤ ጉቱ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቤት የቦታ አዋሳኞች በምዕራብ የህዝብ መንገድ ፣ በምስራቅ የወ/ሮ ብርቁ መኖሪያ ቤት በሰሜን የወ/ሮ አፀደ ገመቹ አዋሳኝ ግቢ በደቡብ የወ/ሮ ብርቁ መውጫ መንገድ የሚያዋስነውን ስፋቱ በግምት 90 ካሬ /ዘጠና ካሬ/ ሜትር የሆነ ይዞታዉ ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥር ያልተሰጠው የመኖሪያ ቤትን የቤቱ አካል ለውል ተቀባይ በብር 9000.00/ዘጠኝ ሺህ ብር/ የሸጥኩለት መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።
2. ውል ሰጪ በዚህ ውል ስምምነት ለውል ተቀባይ የሸጥኩለት ቤት ውል ተቀባይ ሊከፍል የተስማማን ሲሆን በውሉ ደረሰኝነት የሸያጩን ገንዘብ በሙሉ በአንድ ጊዜ ከፍሏል።እኔም ውል ሰጪ የሸያጩን ገንዘብ ብር 9000.00/ዘጠኝ ሺህ ብር/ በሙሉ በአንድ ጊዜ በካሽ ተቀብያለው።
3. በዚህ ውል ስምምነት የሸጥኩለት ቤት የቦታውን አዋሳኝነት ስፋቱ ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተገለፀውን ህጋዊ የቦታ ይዞታዬን ላይ የሰፈረውን ንብረት ባለበት ሁኔታ ለውል ተቀባይ አስረክቤዋለሁ።
4. ውል ሰጪ በሚመለከተው መ/ቤት ቀርቤ በዚህ ውል ስምምነት በሽያጭ ያስተላለፍኩለትን የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ግብሩንና የባለቤትነት ማረጋገጫ በውል ተቀባይ ተዛውሮ እንዲመዘገብ ለማድረግ ተስማምቻለሁ።
5. ውል ሰጪ በዚህ ውል ስምምነት ለውል ተቀባይ በሽያጭ ያስተላፍኩለትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በትክክል የማዝበት ህጋዊ ንብረቴ ስለሆነ ማንም ተቃዋሚ የሌለበት በመሆኑ በዕዳ ይዤዋለው ፣ ያገባኛል ወይም በማንኛውም ሁኔታ ውሉን እቃወማለሁ የሚል ተቀዋሚ /ተከራካሪ/ ቢመጣ ውል ሰጪ መጪውን ወገን በግል ወጪዬ ተከራክሬ ለመመለስ ግዴታ ገብቻለሁ።
6. እኔም ውል ተቀባይ ከዚህ በላይ በተፃፈው ውል መሰረት ተስማምቼ በዚህ ውል ላይ ፈርሜአለው።

<u>ግዴታ</u>

ይህንን ውል ለማፍረስ የሞከረ ወይም በውል የተወሰነውን ግዴታ በአግባቡ ያልፈፀመ ፣ ላለመፈፀም ምክንያት ወይም እንቅፋት የፈጠረ በፍ/ብሄር ህግ ቁጥር 1889/ 1892 መሰረት ውሉን ላላከበረ ኪሳራ ብር 3000.00/ሶስት ሺህ ብር/ ለመንግስት ብር 5000.00/አምስት ሺህ ብር/ ከፍሎ ውሉን የፀና ይሆናል።

<u>ይህንን ውል ስንዋዋል የነበሩ ምስክሮች</u>

1. አቶ ቢቂላ ወርዶፋ
2. ወ/ሮ ጀማነሽ ለማ

3. አቶ ተፈራ ጌታቸው
4. አቶ ደረጀ ኤጀርሳ
5. አቶ ተካልኝ ወርቁ

እኛም ምስክሮች ውል ሰጪና ውል ተቀባይ በዚህ ውል ተስማምተው ሲፈራረሙ ምስክሮችም ሆነን በዚህ ውል ላይ ፈርመናል ። በመሃከላችን ቀደም ሲል የነበረው ውል በዚህ ውሉ ተካቷል።

<u>የውል ሰጪ ፊርማ</u>

1. ----------

<u>የውል ተቀባይ ፊርማ</u>

1. ----------

<u>የምስክሮች ፊርማ</u>

1. ----------
2. ----------
3. ----------
4. ----------
5. ----------